## የእርስዎ መረጃ፡፡ የእርስዎ መብቶች፡፡ ኃላፊነቶቻችን፡፡

**የግላዊ ድርጊቶች ማሳወቂያ**
**ኪንግ ካውንቲ ማህበረሰብና ሰብአዊ አገልግሎቶች**

***የተጀመረበት ቀን: ፌብሩዋሪ 16/2026***

*ይህ ማስታወቂያ እርስዎን የሚመለከቱ የሕክምና መረጃዎች እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውሉ እና ይፋ እንደሚደረጉ ያስረዳል፡፡*

- *የእርስዎ የጤና መረጃ እንዴት ጥቅም ላይ ይውላል እንዲሁም ይጋራል*
- *የጤማ መረጃ በተመለከተ ያሎት መብት*
- *የጤና መረጃ ደህንነት ሚስጥራዊነት ወይ ደህንነት የሚመለከቱ ቅሬታዎች እንዴት እንደሚያስገቡ ወይ መረጃ የሚመለከቱ መረጃዎች*

*እባክዎን በጥንቃቄ ይመልከቱ*
*ይህን ማመልከቻ ኮፒ የማድረግና (በወረቀት ወይም በኤሌክትሮኒክ መልክ) ማንኛውም ጥያቄ ካሎት ኪንግ ካውንቲ ማህበረሰብና ሰብአዊ አገልግሎት ባለስልጣን በስልክና 206-263-6920 ኢሜል DCHS_Privacy@kingcounty.gov ማግኘት ይችላሉ፡፡*

King County

### ክፍል 1፡- የጤማ መረጃ በተመለከተ ያሎት መብት

**የጤና መረጃዎትን በተመለከተ የተወሰኑ መብቶች ይኖርዎታል፡፡ ይህ ክፍል የልዎትን መብቶች እና እኛ እርስዎን ለመርዳት ያሉብንን የተወሰኑ ኃላፊነቶች የሚገልፅ ነው፡፡**

**የጤና መረጃ ቅጂዎን ያግኙ**

- ስለ እርስዎ ያለንን የጤና መረጃ ለማየት ወይ ቅጂ እንዲሰጦት መጠየቅ ይችላሉ፡፡ ይህንን እንዴት ማድረግ እንዳለቦት ይጠይቁን፡፡
- አብዛኛውን ጊዜ የጤናዎን እና የጥቅማ ጥቅምዎን ሰነዶች ከጠየቁን ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረሰ ኮፒውን ወይም ማጠቃለያውን እንሰጥዎታለን፡፡

**የጤና መረጃዎን እንድናስተካከል ሊጠይቁን**

- የጤና መረጃዎ ትክክል ካልሆነ ወይ ያልተሟላ ነው ብለው የሚስቡ ከሆነ እንድናስተካከል ሊጠይቁን ይችላሉ፡፡ ይህንን እንዴት ማድረግ እንዳለቦት ይጠይቁን፡፡
- ለሚያቀርቡሉን ጥየቄ ‹‹አይሆንም›› ልንል እንችላለን ነገር ግን በ60 ቀናት ውስጥ ምክንያቱን በፅሁፍ እንገልፅሎታለን፡፡

**ሚስጢራዊነቱ የተጠበቀ ግንኙነት ይጠይቁ**

- በተለየ መንገድ እንድናገኞት (ለምሳሌ የቤት ወይ የቢሮ) ወይ በመረጡበት አድራሻ ልንልክሎት እንችላለን፡፡
- ሁሉንም አግባብነት የላቸውን ጥያቄዎችን እንቀበላለን፡፡ እኛ አዎ ካላልን አደጋ ውስጥ እንደሚሆኑ ከነገሩን “አዎ” ማለት አለብን፡፡

**የምንጠቀመውን ወይ የምናጋራውን እንድንገድብ ይጠይቁን**

- የጤና መረጃዎችን ለህክምና ለክፍያ ወይም ለእንቅስቃሴአችን እንዳንጠቀም ወይም እንዳናጋራ ሊጠይቁን ይችላሉ፡፡ እርስዎ በሚጠይቁን መስማት አይጠበቅብንም ምክንየቱም የእርስዎን የጤና እንክብካቤ ሊጎዳ የሚችል ከሆነ "አይሆንም" ልንል እንችላለን፡፡
- ከእርስዎ የፅሁፍ ፈቃድ ሳናገኝ ለህክምና ወይ ክፍያ የአደንዛዥ ዕፅ ወይም የአልኮል መጠቀም ችግር መረጃዎን አናጋራም፡፡

### *መረጃ ያጋራናቸውን ዝርዝር ያግኙ*

- የእርስዎን የጤና መረጃ እርስዎ ከጠየቁበት ቀን በፊት ለስድስት ዓመታት ለማን እና ለምን እንዳጋራን ዝርዝሩን (‹‹አካውንቲንግ›› ተብሎ ይጠራል) መውሰድ ይችላሉ፡፡
- ከመደበኛ ህክምና፣ ክፍያና የጤና እንክብካቤ ስራዎችን ከተመለከቱ መረጃዎች ውጪ መረጃዎን ያጋራንበትን ሁሉንም ጊዜዎች የምናካትት ይሆናል፡፡

### በእርስዎ የአሁን እና የወደፊት የአደንዛዥ ዕፅ ወይም የአልኮል መጠቀም ችግር ላይ የተሳተፉ ሌሎች ድርጅቶች እንዲጋራ መጠየቅ

- ለህክምና፣ ክፍያ ወይ የጤና እንክብካቤ ስራዎች ምን ያህል ግዜ የአደንዛዥ ዕፅ ወይም የአልኮል መጠቀም ችግር መረጃዎን እንዳጋራን ዝርዝር የመጠየቅ መብት አሎት፡፡ ይህ ዝርዝርም ጥያቄ ከመጠየቀ ከሶስት ዓመት በፊት ያለውን ጊዜና መረጃዎን ለማን እንዳጋራንና ለምን እንዳጋራን የመሳሰሉት ጥያቄዎች ያካትታል፡፡

### የዚህን የግል መብት ማስታወቂያ ያግኙ

- ምንም እንኳን በኤሌክትሮኒክስ ለመቀበል የተስማሙ ቢሆንም የዚህን ማስታወቂያ ኮፒ በወረቀት መውሰድ ይችላሉ፡፡ የወረቀት ቅጂ እንሰጥዎታለን፡፡

### እርስዎን ወክሎ የሚያስፈፅምሎትን አንድ ሰው ይምረጡ

- ለሆነ ሰው የጤና እንክብካቤ ውሳኔ የመወሰን መብት ከሰጡ ወይ የሆነ ሕጋዊ ተወካይ ካሎት ይህ ሰው በጤና መረጃዎ ላይ ውሳኔ መወሰን ይችላል፡፡
- ምንም አይነት እርምጃ ከመውሰዳችን በፊት ይህ ግለሰብ ስልጣኑን እንዳለ እና በእርሶ ቦታ ሆኖ ጉዳዩን ማስፈፀም እንደሚችል የምናረጋግጥ ይሆናል፡፡

### መብቶ የተጣሰ መስሎ ከተሰማዎት ጥያቄ ያቅርቡ

- መብቶ እንደተጣሰ ከተሰማዎት ቅሬታ ደብዳቤ ወደ 401 Fifth Avenue, Suite 500, Seattle, WA 98104, Attn: የግላዊነት ኦፊሰር ወይም ከዩኤስ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች ቢሮ ለሲቪል መብቶች ቢሮ ወደ 200 Independence Avenue S.W., Washington, D.C. 20201 ደብዳቤ በመላክ፣ 1-877-696-6775 በመደወል ወይም www.hhs.gov/ocr/privacy/hipaa/complaints/ ይጎብኙ፡፡
- ቅሬታ ስላቀረቡ በእርሶ ላይ ቂም አንይዝም፡፡

## ክፍል 2፡- የእኛ አጠቃቀም እና ይፍ አደራረግ:- የእርስዎን የጤና መረጃ በትክክል እንዴት እንደምንጠቀም እና እንደምናጋራ?

### እየወሰዱ ያለውን የጤና እንደክብካቤ ለመቆጣጠር

- የጤና መረጃዎን እንክብካቤ ለሚሰጡት ባለሙያዎች፣ እንክብካቤ የሚያቀናጁት ወይ በቤት ምደባ ላይ ለሚያቀናጁት (መኖርያ ቤት ከሌሎት) ባለሙያዎች የጤና መረጃዎን ልናጋራና ልንጠቀም እንችላለን፡፡
  *ለምሳሌ:- ሽፋን እንድናቀናጅ ወይ ተጨማሪ አገልግሎት ለማቀናጀት አቅራቢው ስለ ህክምና አገልግሎቶ መረጃ ልኮልናል፡፡*
- ቅሬታ ስላቀረቡ በእርሶ ላይ ቂም አንይዝም፡፡

### ድርጅታችንን ለማንቀሳቀስ

- አገልግሎቱን በተሻለ መንገድ ለማቅረብ መረጃዎን ልንጠቀምና ልናጋራ እንችላለን፡፡
  *ለምሳሌ:- የምንሰጣቸው አገልግሎቶች ምን ያህል ውጤታማ እንደሆኑ ለመገምገምና የተሻለ እንክብካቤ የምናቀርብበት መንገድ ለመለየት መረጃዎን ልንገመግም እንችላለን፡፡*

**ለጤና አገልግሎቶዎ ለመክፈል**

- ለጤና አገልግሎቶ ለመክፈል የጤና መረጃዎን ልንጠቀምና ልናጋራ እንችላለን፡፡
  *ለምሳሌ:- ለሚቀበሉት አገልግሎት ክፍያ ከዋሽንግተን ስቴት የማህበራዊ እና የጤና አገልግሎቶች ክፍል እና የጤና እንክብካቤ ባለስልጣን ጋር የእርስዎ መረጃ እናካፍላለን።*

## ክፍል 3:- የእኛ አጠቃቀም እና ይፍ አደራረግ:- የእርስዎን የጤና መረጃ ለሌላ እንዴት እንደምንጠቀም ወይም እንደምንጋራ?

*መረጃህን በሌሎች መንገዶች እንድናካፍል ተፈቅዶልናል ወይም እንገደዳለን። አብዛኛውን ጊዜ ለሕዝብ ጥቅም በሚያበረክቱ መንገዶች፣ እንደ የሕዝብ ጤና እና ምርምር። ለዚህ አላማ የእርሰዎን መረጃ ከማጋራታችን በፊት ብዙ ህጋዊ መስረፈርቶችን ማሟላት አለብን፡፡ ለበለጠ መረጃ:* www.hhs.gov/ocr/privacy/hipaa/understanding/consumers/index.html *ይጎብኙ*

**የህብረተሰብ ጤናና ደህንነት ችግሮችን ለመፍታት እገዛ ለማድረግ**

ስለ እርስዎ የጤና መረጃ ለሚከተሉት አላማዎች ልናጋራ እንችላለን:

- በሽታ ለመከላከል፡፡
- የተጠረጠረን ጥቃት፣ ማግለል ወይም የቤት ውስጥ ትንኮሳን ርፖርት ለማድረግ፡፡
- በማንኛውም ሰው ጤናና ደህንነት ላይ ከባድ ስጋት ለማስቀረት፡፡

**ለምርምር ጥናት**

የእርስዎን መረጃ የጤና ምርምር ለማካሄድ ልንጠቀምበት ወይም ልናጋራ እንችላለን፡፡

**ህግን ለማክበር**

DHHS የፌደራል የግላዊነት ህግን የምናከብር መሆናችንን ማየት ከፈለገ ከጤና እና ሰብአዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት (DHHS) ጋር ጨምሮ የስቴት ወይም የፌደራል ህጎች የሚያስፈልጋቸው ከሆነ ስለእርስዎ መረጃ እናጋራለን።

**የሰራተኞችን የካሳ ችግሮች፣ የህግ አፈፃፀም እና የመንግስት ሌሎች ጥየቄዎች ላይ ምላሽ ለመስጠት**

ስለ እርስዎ መረጃ ለሚከተሉት ልንጠቀም ወይም ልናጋራ እንችላለን:

- ለሰራተኞች ካሳ ጥያቄ፡፡
- ሕግ ለማስከበር ዓላማ ወይ ለህግ አስከባሪ አካላት በተወሰነ ሁኔታዎች ላይ ላይ የረገደባል፡፡
- ለጤና ተቆጣጣሪ ኤጀንሲዎች ህጉ ለሚፈቅደው ተግባር፡፡

**ለክስ ወይም ህጋዊ እርምጃ ምላሽ ለመውሰድ**

ለፍርድ ቤት ወይም አስተዳደራዊ ትእዛዝ ወይም ለምስክርነት ምላሽ ለመስጠት የእርስዎን የጤና መረጃ ልናጋራ እንችላለን፡፡

**አጠቃቀም እና ይፋ አደራረጋችን**

በዚህ ማስታወቂያ ውስጥ ያልተገለጹ ሌሎች አጠቃቀሞች እና መግለጫዎች የሚደረጉት በጽሁፍ ፈቃድ ብቻ ነው።

## ክፍል 4: የአደንዛዥ ዕፅ ወይም የአልኮል መጠቀም ችግር መረጃ መጠቀምና ማጋራት

የአደንዛዥ ዕፅ ወይም የአልኮል መጠቀም ችግር መረጃ ምስጢራዊነት ለበለጠ አጠቃላይ ጤና መረጃ ከተሰጡት መመሪያዎች የበለጠ ጥብቅ በሆኑ ደንቦች የተጠበቀ ነው። ለምሳሌ ለህክምና ዓላማ፣ ለክፍያ ዓላማ ወይ በፅሁፍ ፈቃድ ሳይሰጡን ድርጅታችን ለማስተዳደር የአደንዛዥ ዕፅ ወይም የአልኮል መጠቀም ችግር መረጃ ማጋራት አንችልም፡፡

**የፍቃድ መሰፈርት**

- ሁሉንም የወደፊት አጠቃቀሞችን ወይም መረጃዎችን ለህክምና፣ ለክፍያ እና ለጤና እንክብካቤ ስራዎች ይፋ ማድረግን የሚያካትት አንድ ፈቃድ መስጠት ይችላሉ።
- በፅሁፍ በማንኛውም ሰዓት ፈቃድዎን መሰረዝ ይችላሉ፡፡ ይህ ማስታወቅያ እንደደረሰን የምንሰርዘው ይሆናል፡፡ ከዚህ በፊት በሰጡት ፈቃድ የተጠቀምነው ወይ ያጋራነው መረጃ ላይ ለውጥ አይኖርም፡፡
- በእርስዎ ፈቃድ መረጃው ከተጋራ ይህ መረጃ የሚደርሰው ማንኛውም ሰው ይህን ተመሳሳይ የሚስጥራወነት ሕግን መከተል አለበት፡፡ ያለእርስዎ ፈቃድ ዳግም ሊያጋሩት አይቸሉም፡፡

**በፈቃደኝነት ማጋራት**

በሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ ከሆነ የአደንዛዥ ዕፅ ወይም የአልኮል መጠቀም ችግር መረጃ እንድናጋራ ይፈቀዳል ወይ ይገደዳል፡

- በድንገተኛ አደጋ ጊዜ ለህክምና ባለሙያ
- የህፃናት ጥቃት ወይ ቸልተኝነት ተጠርጣሪ በተመለከተ
- የተጠረጠሩ የወንጀል ድርጊቶችን ሪፖርት ለማድረግ
- ለምርምር፣ ለኦዲት ወይም ለግምገማዎች
- በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሲፈለግ
- በተፈቀደው ስምምነት መሰረት ብቃት ካለው የአገልግሎት ድርጅት ጋር ሲሰራ

የአደንዛዥ ዕፅ ወይም የአልኮል መጠቀም ችግር መረጃ ጋር የተያያዙ ሌሎች መረጃዎች የምናጋራውና የምንጠቀመው ከእርስዎ የፅሁፍ ፈቃድ ካገኘን ብቻ ነው፡፡

**በህጋዊ ሂደቶች ውስጥ መረጃዎን ከመጠቀም የሚከለከሉ ነገሮች፡-**

- የአደንዛዥ ዕፅ ወይም የአልኮል አጠቃቀም ችግር - ወይ ይህን መሰረት ያደረገ ምስክርነት ፍርድ ቤት ትእዛዝ ካልሰጠ ወይ በፅሁፍ ፈቃድ ካልሰጡ በስተቀር ፍርድ ቤት ውስጥ ጥቅም ላይ አይውልም፡፡
- የፍርድ ቤት ትእዛዝ ከደረሶት ስለዚህ ሊያሳውቆት እና ፈቃድ እንዲሰጡ እድል ሊሰጡዎት ይገባል፡፡
- የፍርድ ቤት ትእዛዙ ይህን መረጃ ማጋራት ትእዛዝ ለማስፈፀም መጥርያ መያያዝ አለበት፡፡

## ክፍል 5: ኃላፊነቶቻችን

**የጤና መረጃ ሚስጥራዊነትና ደህንነት መረጃ**

- በህግ የጤና መረጃዎ ሚስጥራዊነትና ደህንነት እንድንጠብቅ እንገደዳለን፡፡
- የእርስዎንመረጃ ሚስጢራዊነት ወይ ደህንነት ሊነካ የሚችል ጥፋት ከተፈጠረ ወዲያውኑ እናሳውቆታለን፡፡ በፌደራል ደንብ መሰረት የፌደራል ሕግና ደንብ ጥሰት ወደ ተገቢው አካል ሪፖርት የሚደረግ ይሆናል፡፡
- እኛ በዚህ ማስታወቂያ ውስጥ የተቀመጡትን ግዴታዎች እኛ የሚስጢር አጠባበቅ መከተል እና እርስዎ ሲጠይቁ ኮፒውን ለእርስዎ መስጠት ይኖርብናል፡፡
- እርስዎ መጠቀም እንደምንችል በፅሁፍ ካላሳወቁን በስተቀር የእርስዎን የጤና መረጃ በዚህ ውስጥ ከተገለፀው አላማ ውጪ አንጠቀምም ወይም አናጋራም፡፡ እርስዎ ከፈቀዱልን እንችላለን፡፡ ነገር ግን ሀሳብዎን በመማንኛውም ጊዜ መለወጥ ይችላሉ፡፡ ሀሳብዎን ከለወጡ በፅሁፉ ይግለፁልን፡፡

**ዳግምማጋራት፡**

- አንዴ ከተጋራ በኋላ ይህ መረጃ የደረሰው አካል ዳግም ሊያጋራው ይችላል ይህም መረጃ በተመሳሳይ ሕግ ላይጠበቅ ይችላል፡፡

***በዚህ ማስታወቂያ ቃሎች ላይ የሚደረግ ለውጥ***

የዚህን ማስታወቂያ ቃሎች መቀየር ይምንችል ሲሆን ለውጡም ስለእርስዎ ባለን ማንኛውም መረጃ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡ አዲሱ ማስታወቂያ በጥያቄ እና በድረ-ገፃችን ላይ ይገኛል እና ቅጂውን በፖስታ እንልክልዎታለን።

## ክፍል 6: ተጨማሪ መስረጃ

ለበለጠ መረጃ:-

- www.hhs.gov/ocr/privacy/hipaa/understanding/consumers/noticepp.html.
- Fact Sheet 42 CFR Part 2 Final Rule | HHS.gov

**የኪንግ ካውንቲ የማህበረሰብ እና የሰዎች አገልግሎቶች መምሪያ**
**ሚስጥራዊነት ኦፊሰር (206)-263-6920**
**401 Fifth Avenue Suite 500, Seattle, WA 98104**
**ኢሜይል፡ DCHS_Privacy@kingcounty.gov**